# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ.39 ቁ. 6 ሚያዚያ 2006 ዓ.ም

## ሕዝብን ለመስዋዕትነት የጠራ ችግር ሳይወገድ ትግል አያቆምም !

የኅብረተሰብ እድገት፤ ቅራኔና ሂደትን መረዳት ያልቻሉ የሕዝብ አመጽና ፍንዳታ በጥቂት ተንኮለኞች ሴራ የሚመጣ ይመስላቸዋል። እነዚህ ሰዎች በአጼው በሥርዓት ላይ ጎርፍ እየመጣ ባለበት ጊዜ ችግሩን የፈጠሩትና የሚያባብሱት ጥቂት "በፈተና የወደቁ" የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ናቸው የሚለውን ክስ ሲደረድሩ ባጅተው ነበር። የሚያሳዝነው ዛሬም ቢሆን የነበረውን ችግር ሁሉ--የኤርትራን ጉዳይ ሳይቀር-- ያ ትውልድን ኢሕአፓ ፈጠረው ብለው አላዋቂነታቸውን የሚያጋልጡ አሉ። ሕብረተሰብ ሂደቱ የራሱ ሕግ አለው። ቅራኔዎች ባለው ሥርዓት የሚወሰኑ ናቸው። ቅራኔዎቹ ሲበስሉና የሚረግቡበት ሁኔታ ሲጠፉ ፍንዳታ መከተሉ አይቀሬ ይሆናል። ያኔ ሕዝብን የሚያቆመው ኃይል ከቶም አይኖርም። ሕዝብም ቀይዶ ይዞት ከነበረው የንቃተ ህሊና ማነስና ከፍርኃቱ ይላቀቃል። ሞት አይፈሬ ሆኖ ለመስዋዕትነት ይነሳል ። በየካቲት 66 የፈነዳው የሕዝብ አብዮት ይህን ሂደት የተከተለ ነበር።

የየካቲት አብዮት የፈነዳው በገዢው መደብና በሕዝብ መሐከል የነበረው ቅራኔ ከማይታረቅበት ደረጃ በመድረሱ ነው። በሥልጣን ላይ የነበሩት ክፍሎች ጊዜያቸው ማለቁን ባለመረዳታቸው የሕዝቡ አመጽ የሽሮ ተክ ተክ ብቻ መስሏቸው፣ በአጭሩ የሚረግብ ነው ብለው ደመደሙ። የ1953 ዓ.ም. የነመንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥቱ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ተቀብለው ማድረግ ያለባቸውን፤ የሚገባቸውን ተገቢ ለውጥ ቸል ከማለታቸው ሌላ ሁኔታው በሕዝብ--በተለይም በተማሪዎች-- መንፈስና ንቃት ላይ ያደረሰውን ጫና ሊገነዘቡት አልቻሉም። አብዮቱ እንደ ክረምት ጎርፍ ድንገት አጥለቀለቃቸው-- አንደምታውንም በቅጡ ሳይረዱ ውድቀታቸው በአስከፊ መልኩ ተከሰተ። የየካቲትን አብዮት ግብታዊ ነው ማለቱ የተለመደ ቢሆንም ይህ ድምዳሜ ትክክል አይደለም ። አብዮቱ የፈነዳው ቦግ ጭልም ሲል በቆየና ለረጅም ጊዜ በሕዝብ በተካሄደና የደም ዋጋ ሲከፍልም በቆየ ትግል ነው።

በተለያዩ አካባቢዎች በተናጠል በተለያዩ ጥያቄዎች ዙሪያ ይደረጉ የነበሩ አመፆችና ተቃውሞዎች የመደራጀት ጥያቄን አጉልቶ በፖለቲካው መድረክ የመወያያ ርዕስ አደረገው። ይህንን ሁናቴ በወቅቱ የተገነዘቡትና ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረከቱ የዛ ትውልድ ብርቅዬ አባላት ኢሕአፓን በ1964 ዓ.ም ለመመስረት ረግረጉ ተመቻቸላቸው። በሂደቱም በርካታዎች ለመቀላቀል ዕድሉን በማግኘታቸው ተሰበጣጥረው የነበሩትን ትግሎች ለማቀናጀትና፤ አመራርና አቅጣጫ ለመስጠት የኢሕአፓ መመሥረት መልካም አጋጣሚ ፈጠረላቸው። በዚህም በርካታ ድሎችን ለመጎናፀፍ አስችሏቸዋል። አንጋፋ የተባለውን ቅጽል ኢሕአፓ ሊጎናፀፍ የቻለውም ሚስጢሩ ይኸው እንጂ ሌላ አይደለም።

በአሁኑ ወቅት 42 አመት ወደኋላ ተመልሰን ሁናቴውን በሕሊናችን ስንቃኘው ለአብዛኛው ሕዝብ የህልውና ጉዳይ የነበረው መሬት አልባነት፤ ጪሰኝነትና ገባርነት ለበርካታ የአርሶ አደሩ አመጽ ምክንያት ሆኖ መቆየቱን እንገነዘባለን። የመሬቱ ጥያቄ ደግሞ ሊካድ በማይችለውና በነበረው የብሔረሰብ ጥያቄ የታጀበም ነበርና ያስነሳው የአርሶ አደር አመጽ የሚበርድ አልነበረም። ዛሬ ታሪክን በጭፍን መሰረዝ የበርካታዎች ልምድና አቋም ሆኖ ተገኝቷልና በዚያን ጊዜ በሃይማኖት ረገድ አድልዎ፤ በብሔረሰብ ደረጃ ልዩነት የለም ብለው ሊክዱ ቢጥሩም የነበረው የጭቆና ሐቅ አሌ ይላቸዋል። የአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነትና መብት ጥያቄ ዋናው የሕዝብ መፈክር ሆኖ፤ በተማሪዎች "መሬት ለአራሹ!" በሚል ተስተጋብቶ እነሆ እስከዛሬ ምላሽ ያጣ ጥያቄ ሆኖ አለ። በላብአደሩ በኩልም ማኅበሩን ለመመሥረት ሲታገል፤ አድማ ሲመታና ሲጠቃ እንደነበርም (የእነአቶ አበራ ገሙን መስዋዕትነት ያስታውሷል) የሚታወቅ ነው።

የአጼው ሥርዓት በተለይ ከጣሊያን ወረራ በኋላ የራሱን ውድቀት በአንጻራዊ ፍጥነት መጋበዙ የሚመዘገብ ነው። ይህም የቀድሞ መኳንንቶች ይሉ እንደነበረው ለ " መናጢ ድሀ ልጆች " ትምህርት ቤት በመክፈቱ ሳይሆን መሠረቱ በጭቆናና ብዝበዛ ላይ በመሆኑ ነው። ይባል እንደነበረው የፊውዳሎች ወይም (ስያሜው ትክክል ባይሆንም ) ባላባታዊ መንግሥት ስለነበርና በመደብ ልዩነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከሥረ መሠረቱ ከሕዝብ የተጣላ ነበር። ከነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅል ሙከራ በፊትም የእነ ቢትወደድ ነጋሽ ነበር፤ ከነገርማሜም በኋላ በርካታ ሙከራዎችም ቀጥለዋል። በባሌ፤ በነገሌ፤ በኦጋዴን፤ በደራሳ ከዚያም በጎጃም የነበሩት ደም ያስፈሰሱ አመጾች የሚረሱ አይደሉም። በትግራይ ቅኝ ገዢ እንግሊዞች ፍውዳሎቹን (ባላባቶቹን)ና ንጉሣዊ ቤተሰብ ነበርን ባዮቹን ቆስቁሰው ያስነሱትን አመጽ (ዛሬ ወያኔ ቁጥር አንድ ወያኔ የሚለው) ከድተው ከኤደን (የመን) ባመጡት አይሮፕላን ቢደበድቡም ዘውድ ተቀማን ባዮቹ አርሶ አደሩን በአጼው ላይ ለማስነሳት ሰንፈው አያውቁም ነበር፡፡ ይህንኑ ስሜትና ቁርሾ ወያኔም ጸረ ሸዋ ባለው ጸረ አማራው ትግሉ ተጠቅሞበታል፤ ዛሬም ይህ ጸረ አማራ ስሜቱ ቤንዚኑን የሚያገኘው ከዚያው መሆኑም የሚታይ ነው።

የኦጋዴንና የኤርትራ አመጾችም --በተወሰነ ደረጃ የባሌም--የብሔር ጥያቄ ሊባል የበቃውን ይዘው የተነሱ ለመሆናቸው ሀቅን አፋኞች ምንኛ ቢንፈራገጡ ሊለውጡት ያልተቻለ ነው። የኤርትራው የኢድሪስ አዋቴና የጀብሐም አመጽ የጀመረው በ1953 ዓ.ም. ሲሆን ዛሬ ኤርትራን ለግንጠላ ቆሰቆሰ ተብሎ በታሪክ ላጺሶች የሚከሰሰው ተማሪ/ትውልድ የረባ የለውጥ እንቅስቃሴን ያበሰረው በ1958 ዓ.ም በመሬት ለአራሹ ሰልፍ ነበር። አንዳንድ ለጥቅማቸው ያደሩ ግለሰቦች ውጉዝ ከመ አርዮስ በማለት የሚኮንኑት ኢሕአፓማ የተመሠረተው በ1964 ዓ.ም ነበር። የአጼው ሥርዓት ፌደሬሽን የተባለውን ማፍረሱና ለአንድነት የታገሉ ኤርትራውያንን ጣል ጣል በማድረጉ ለአመጹ መስፋፋት--ከነግብጽና አረቦች ባልተናነሰ-- አስተዋጽዖ አደረገ። ደርግም ሰሀን መሽጫ ሱቅ እንደገባ ደንባራ በሬ ግራ ቀኙን አተራምሶ፤ ችግሩን ከመፍታት አንጻር ብዙ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይችሉ የነበሩትን ጀኔራል አማን አንዶምን ገድሎ፤ በሰላምና በድርድር ችግሩ ይፈታ ያሉትን ሁሉ በክህደት አውግዞ ወደ ጦርነት በማምራቱና በአሥመራ ከተማ እስራኤል ባሰለጠነቻቸው ኮማንዶዎች በማሳነቁና ወጣቱን ወደ በርሃ በማስኮብለሉ ችግሩን አባባሰውና ለአማጽያኑ ከፍተኛ ጥቅም አበረከተ። ከዚያም ወዲህ ቀይ ኮከብ ዘመቻ ቢል፤ እናት ሀገር ጥሪ ሚዛኑን ሊለውጠው አልቻለም። ኮብላዩና አረመኔው ኮሎኔልም የራሱን መኮንኖች በመጨረሱና መፈንቅል ሞከረቡኝ ብሎ አያሌ ጀነራሎችን በመፍጀቱ ሥልጣኑንም ኤርትራንም ለገንጣዮቹ አስረከበ። የሥርዓቱ ጥፋትና ድክመቶች

ናቸው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ያደረጓት እንጂ ለኢትዮጵያ የታገሉትና የተሰዉት ወጣቶችና ታጋዮች አልነበሩም። ለዘመናዊ ባንዳዎችና ሹምባሾች አልዋጥ ያላቸው ይህ ሐቅ ነው። በኡም ሐጀር፣ በባሴ፣ ...ወዘተ የተደረጉትንም ጭፍጨፋዎች መስማት አይፈልጉም።

ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስረሳ ሆነና፤ ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል የተባለውም ችላ ተባለና ዛሬ ኃይሌ ኃይሌ የሚሉት ሁሉ --አውቀውም ሆነ ባለማወቅ-- ያን ግፈኛ ሥርዓት ቅቤ እየቀቡና በተፈጀው ሕዝብ ደም እየቀለዱ መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል። መንጌ፣ መሌ ባዮችም ተመሳሳይ ማፈሪያዎች ናቸው። የአጼው ጊዜ ገባሩ ሕዝብ ሁለት ሶስተኛ ምርቱን ለባላባቶቹ ማስረከብ እንዳለበት በህግ የተደነገገ ሲሆን አርሶ አደሩ ያጣ የነጣ ሆኖ ለአስከፊ ርሃብ ተጋልጦ ማለቁ ደግሞ የሩቅ ዘመን ትዝታ አይደለም። የአርሶ አደሩን መሠረታዊ "መሬት ለአራሹ" የሚለውን ጥያቄ ተገቢውን ዴምክራሲያዊ መፍትሔ በመስጠት ፈንታ ደርጉ መሬትን በማገርና የመንግሥት በማለት (የማ መንግሥት የሚለው አቢይ ጥያቄ ሕዝባዊ ምላሽን በተነፈገበት) አርሶ አደሩን የመንግሥት/የደርግ ጢሰኛ አደረገው። የኮታ መንግሥት ዕውን ሆነ፤ የገበሬው ድህነትና መከራ አየለ። ረሃቡ ተስፋፋ፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በረሃብ ማለቁ ቀጠለ። በግዳጅ ዘመቻና በብሔራዊ ውትድርና አርሶ አደሩን ቆላው።

በግዳጅ ሰፈራም አደኸየው፣ ጨረሰው። በወያኔም የቀጠለው ተመሳሳይ ነው --መሬት የሕዝብ ተብሎ ወያኔና ሕዝብ ተወራራሽ ቃላት ሆነው ተከሰቱ። ዛሬም የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ዋናና አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ የጊዜያችንም ትግል ዋና መፈክር ሆኖ ቀጥሏል። ለሕዝብ ጥቅም፣ መብትና ለዴሞክራሲ የታገሉት ተማሪዎችና ተራማጆች ያነሷቸው መሠረታዊ የህዝብ ጥያቄዎች ትግሉን ለማቀጣጠልና የአጼውን ሥርዓት ውድቀት ለማምጣት ትልቅና የሚያኮራ ሚና ተጫውተዋል። ዛሬም ተመሳሳይ ሚና ይኖራቸው ዘንድ ሲጠበቅ ጋሬጣ የሆነው ወያኔ ያሰፈነው የጎጠኝነትን ክፍፍል መሆኑ ደግሞ ግልጽ ነው።

አብዮትን አንፈልግም ስላሉት አይቀርም--ሞኞች ይሞኛሉ እንጂ። የሕዝብ አመጽም የተንኮል ውጤት ሳይሆን የሥርዓት መበስበስ መዛባት የሚያመጣው ነው። የአጼው አገዛዝ መውደቅ መዘግየቱና ጊዜ መፍጀቱ ነው አስገራሚ የነበረው። አብዮቱ ግን በኢዴሞክራሲያዊ መኮንኖች ስለተደናቀፈ የሕዝብ ፍላጎት ሳይሟላ ቀረ። ፋሺስታዊ መኮንኖች--ዛሬም ቢሆን ጭራቅነታቸውን መገንዘብ ያልቻሉ ወደ ሥልጣን መጡ--ትግሉም እንደዚያው ቀጠለ። ያኔም ቢሆን በ1983 ዓ.ም ደም የጠማው ማንም ሀገር ወዳድ አልነበረም። አለመታገል ግን ቃል ኪዳንና ሀገርን መክዳት በመሆኑ ቆራጡ ትውልድ ትግሉን ቀጥሎ ከፍተኛ መስዋዕትነትንም ተቀበለ ። ይህ ትውልድም በዚያው ልክ ገንጣዮችን እየታገለ ሲሰዋ ዛሬ ዋና ጸረ ገንጣይ ነን ይሉ ያሉት ደግሞ ድምጻቸው አልተሰማ ደብዛቸው አልተገኘ ነበር ብንል ስህተት አይሆንም። ደርግም ሀገርን ለውድቀት ዳርጎ፤ ለግንጠላ አመቻችቶ አከተመ። አረመኔ መሪዎቹም በየአቅጣጫው ፈረጠጡ። ሕዝብን ለአብዮት፣ ለማነሳሳት፣ ለመረረ ትግልና መስዋዕትነት ያበቁት ችግሮች ሁሉ ሳይፈቱ ስለባጁም እነሆ ዛሬም ትግሉ መቀጠሉ የግድ ሆኖ መሬታችን የዜጎቻችንን የመስዋዕት ደም ጠያቂ ሆናለች። መሬት ለአራሹ፤ ድሃው ይማር፤ ድህነት ወንጀል አይደለም፤ ሠርቶ አደሩ ላቡና መብቱ ይከበር፤ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ይመሥረት፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ይከበር፤ የሕግ የበላይነት ይረጋገጥ፤ እኩልነት ይስፈን፤ የሃይማኖት አድልዎና ልዩነት ያክትም፤ ...ወዘተ ብሎ የተነሳው አብዮት ከግብ አልደረሰም። በ1966 አብዮት ክርስቲያኑና እስላሙ፣ ወንዱ ሴቱ፣ ወጣቱና አዛውንቶች፤ ሲቪሉና ወታደሩ ሁሉ በጋራ ታግለው ለአገዛዙ ውድቀት አስተዋፅዖ አድርገዋል። የሕዝብ ኅብረት የታየበት አብዮት ነበር--ሁሉም በደሉና ቁስሉ ይሰማው ነበርና ነው። ደርግ ባካሄደው አረመኔያዊ ሽብርና ጭፍጨፋ የበላይነትን

ቢይዝም የትግልን ወገብ ሊሰብር ባለመቻሉ በተራው ወደ ውድቀቱ አመራ--ያውም ካለፈው ከፍቶ። የአጼውን ዘመን አቀባባይ ከበርቴዎች በራሱ መንግሥታዊ ከበርቴዎች ቢተካና የማይበጀውን የሶቭየት ይዞታ ቢቀዳም በሀገራችን ለሀገራችን ዕድገት የተሻለ ሊሆን የሚችለውን ብሔራዊ ከበርቴ አጫጫው እንጂ ኣላጎለበተውም። ሀገራዊ ብሔራዊ ኤኮኖሚ ይገንባ የሚለው ጥያቄ ተኖ ቀረ። ወያኔ ደግሞ ካለፉት ሁለት ሥርዓቶች በባሰ የሀሪቷን ኤኮኖሚ ለራሱ ያውም በጎጠኝነት ደረጃ ይዞ ሀገራችንን ለባዕዳንም ሸጠ፤ ሰጠ። በሁሉም ሉዓላዊነት አፈር በላ- የአጼውን አሜሪካ የደርግ ሶቭየት ሲተካ ወያኔ ደግሞ ተመልሶ ለአሜሪካና በቅርጫው አለን ላሉ ሁሉ ሸጣት። በኅብረተ ሰብ ደረጃ፤ በማኅበረሰብ ደረጃ ውድቀትና ድህነት የሕዝባችን ዕጣ ሆኖ እስካሁንም አለ።

ወያኔ ዛሬ የሚደረድረው የእድገት አሃዝ ከንቱ መሆኑ በገሃድ የሚታይ ሲሆን እውነታውን ወዳጆቹም አልካዱትም። ይህንንም የምናየው ነው። ሀገራችን ሚሊዮኖች የሚራቡባት፤ ብዙ መቶ ሺዎች መጠለያ ያጡባት፤ የተሰደዱባት ስትሆን፣ ጥቂቶች ባለ ሚሊዮን ሆነው ጉርሻ እንኳን የማያገኘው ደግሞ ብዙ መቶ ሺ መሆኑ አገራችን ላለችበት አስከፊ ሁኔታና ለደረሰው ውድቀት ምስክር ነው። ብዙሃኑን ገበሬና አርሶ አደር ከጪሰኝነትና ከብዝበዛ ለማላቀቅ በ "መሬት ላራሹ" ሥር እልህ አስጨራሽ ትግል ተካሂዶ የባላባት ሥርዓት እንዲገረሰስ ቢደረግም ደርግ የሚባል አረመኔ ቡድን የሕዝቡን ድል ቀምቶ የራሱን አምባገነናዊ ሥርዓት በመመሥረቱ በሥልጣን በቆየበት 17 አመታት ውስጥ የመሬቱና የምርቱ ባለቤት የመሆን መብት ግን አልተረጋገጠለትም። ይብሱኑ መሬት ለአራሹ የሚለው መሬት በሕዝብ ሥም በወታደራዊ አገዛዝ ተተካ። ሲጠላውና ሲቃፈው የነበረው ለአመፅ ምክንያት የነበረው ጪሰኝነቱ በሌላ መልኩ እንዲቀጥል ተደረገበት። ትግሉ ግን ቀጥሎ የደርግ አገዛዝ ቢደረመስም ጪሰኝነቱን በባሰ ሁኔታ ያስቀጠለበት የባሰ ከፋፋይና ጎጠኛ የሆነ ቡድን ወያኔ በሥልጣኑ ተኮፈሰበት።

ይህም በመሆኑ መሬት ለአራሹ የሚለው የትግል መፈክር መሠረታዊ ይዘቱ አርሶ አደሩን ከብዝበዛ ማላቀቅ፤ በሚያርሰው መሬት ላይ ብቻ ሳይሆን ጥሮ ግሮ በሚያመርተው ምርትና ግላዊ ንብረቱ ጭምር ለመወሰን ባለ ሙሉ መብት ለማድረግ፤ የእናውቅልሃለን አባዜ የሚጠናወታቸው የሱ የበላይ ጠባቂና ወሳኝ ከጫንቃው ላይ እንዳይቆናጠጡበት ለመከላከል፤ በሀገሩም ሆነ በራሱ የወደፊት እጣ ላይ እንደ ሌሎቹ የማህበረሰብ ክፍሎች ሁሉ በእኩልነት የበኩሉን ተገቢ ድርሻውን እንዲያበረክት ለማስቻል ነበር። አሁንም ነው። መሬት ላራሹ የሚለው የሀገር ባለቤትነትንም ገላጭ ነውና የተወሰነ አካባቢን እንዳሻ ለአንድ ብሔር በብቸኛ ባለቤትነት አሳላፎ ሰጥቶ በተጨቆኑ ብሔሮች ስም ሌላ አዲስ ፈላጭ ቆራጭ ለማንገስና የሌሎች ብሔር አባላትን ለምሳሌ የአማራ ብሔራ ተወላጆችን በጠላትነት በመፈረጅ በቂያቸው ጭራሱኑ የመሬት ባለቤትነትን ነፍጎ ለማባረር መሳሪያ ለማድረግ አይደለም። አርሶ አደሩ በእኩልነትና በነፃነት መርህ ላይ መመሥረት ከነበረበት ፌዴሬሽን በተለየ በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ነገር ግን በጨቋኝነትና በሙብት ረጋጭነት ካለፉት በባሰ አገዛዝ ሥር እንዲወድቅ ተደርጎ ፍዳውን የሚያይበት ሁኔታ ተፈጥሮበታል። በዚህም የተነሳ አርሶ አደሩ የመሬቱ ባለቤት ለመሆን አለመቻል ብቻ ሳይሆን ይባስ ብሎ መሬቱን እየተነጠቀ ተሳዷል፤ ተፈናቅሏል። መሬት ለባዕዳን ተሸጧል፤ ለሱዳን ተሰጥቷል። በመሆኑም መሬት ለአርሶ አደሩ ዋነኛውና መሠረታዊ የኑሮው ወይንም የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥያቄ ነውና ዛሬም እንደ ቀድሞው አርሶ አደሩንና ገበሬውን የመሬት ባለቤት ለማድረግና በነፃ የመደራጀት መብቱ እንዲከበር መታገል መሠረታዊ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

በማኅበረሰብ ኑሮ ደረጃም ያለው መከራ የሚታወቅ ነው። ሕጻናት ሳይቀሩ ለሙት ተዳርገዋል፤ ወጣት ሴቶች ለዘመናዊ ባርነትም ተልከው በዘረኝነት በመሰቃየት ላይ መሆናቸውን የነሳውዲ፣ ቃታርና ሌባኖን ግፍ ይገልጸዋል። መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ሥር ሊሰዱ ቀርቶ ደብዛቸው ተፈልጎ አይገኝም። ዜጎች ከሕግ ውጭ የተለያዩ ምክንያቶች እየተፈጠሩ በቁጥጥር ሥር ይውላሉ፤ ደብዛቸው እንዲጠፋ ይደረጋል። ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ዜጎች በተለይም የሥርዓቱ ተቃዋሚ ተብለው የሚጠረጠሩ እንዲታሰሩና እንዲታፈኑ ይደረጋሉ። አድልዖ በጣም የሰፈነ በመሆኑ በፍትህ ጉድለት የሚሰቃየው የዜጋ ቁጥር በርካታ ነው። ሙስና በጣም ከመባባሱ የተነሳ የሕዝብ የነቀርሳ በሽታው ሊሆን በቅቷል። የኑሮ ውድነቱ፣ የዋጋ ንረቱ፣ ከጅ ወደ አፍ ለሚኖረው ብዙሃኑ ሕዝብ ቀርቶ መለስተኛ ገቢ ላለው መካከለኛ ክፍል እንኳ ለመቋቋም እየቸገረው ያለበትን ሁኔታ በወያኔ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳዎች ተነው እንዲጠፉ አልሆኑም። ተቀጥሮ የሥራ ደሞዝ ለማግኘት እድለኛ የሆነ ዜጋ እንኳ ሳይቀር በአግባቡ አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ እህሎችን ሸምቶ ቤተሰቡን ቀርቶ ራሱንም በግል ደረጃ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚችልበት አቅም እያጣ ያለበት መሆኑ በገሃድ የሚታይ ነው። በርካታው ሕዝብ አሁንም ከድህነት ወለል በታች ለመኖር መገደዱ ብቻ ሳይሆን ገነባን አስገነባን እያሉ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲሉ በቁጥጥራቸው ባሉት የዜና ተቋማት እንዲታዩ ከሚያደርጓቸው ግንቦች ጀርባና ከመንገዶች ጥግ ባሉ ጢሻዎች ለመኖር የተዳረጉ በርካታ ዜጎዎችን ማየቱ የሥራቸው ውጤት ናቸውና ለማየት ይቀፉቸዋል። ልጆቹ ሲራቡ ለማብላት፣ ሲታመሙ ለማሳከም፣ ተንከባክቦ ለማስተማርና ለአቅመ አዳም ለማድረስ አቅም ያጣው የዜጎች ቁጥር ግምቱ ከፍተኛ ሲሆን በሚከተሉት ፖሊሲ ምክንያት ችግሩን ለመቅረፍ የማይቻል በመሆኑ ተባብሰው ቀጣይ መሆናቸው ግልፅ ነው። በርግጥም በወቅቱ ሰፍኖ ያለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ በኢሕአፓና በሀገር ወዳድ ዜጋ ሲቃኝ ኢትዮጵያና ሕዝቧ በጣም አሳሳቢና አደገኛ ሁኔታ ላይ መሆናቸው እሙን ነው።

የጤና ሥርዓቱ በአግባቡ አለመስፋፋቱ እንዳለ ሆኖ  የሕክምና ባለሙያዎች፤ መሳሪያዎችና መድኃኒቶች በሚያስፈልጉት ደረጃ ለማዳረስ ባለመቻሉ የባኅል ኃኪሞችን የሚያዘወትረው ዜጋ ቁጥሩ እየጨመረ ይገኛል። የጤነንት ሁናቴን በመጠበቅ ሊወገዱ የሚችሉ ቀላል በሽታዎች የሚጠቃውና ለሞት እየተዳረገ የሚገኘው ዜጋ  በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከፍተኛ ነው።  ለሕክምና ምርመራ የሚጠየቀው ዋጋ ብዙሃኑ በወር ከሚያገኘው ቋሚ ደሞዙ - ያውም ሥራ ለማግኘት እድሉን ካገኘ-  በጣም ከፍ ያለ ነው። በዚህም የተነሳ የጤና ተቋማትንና ኪሊኒኮችን መጎብኘት ቀርቶ ባጠገባቸው ማለፉ እንኳ የሚሞከር አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ እያሳረፈ ያለው ችግር እንዳለ ሆኖ ከውጭ ንግድ መቀነስ፣ የኤሌክትሪክና የውሃ አቅርቦት ቀውስ፣ የሲሚንቶና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተዳብሎበት ባልጠበቀው ሁኔታ በሡርቶ አደሩ ሕብረተሰብ መካከልም የራሱን አሉታዊ አስተዋጽዖ ያሳረፈ በመሆኑ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የሕዝቡን ችግር ይበልጥ አባብሶታል።

ዛሬም ከ 23 አመት በኋላ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲመገብ እናደርጋለን ተብሎ በተፎከረበት ሀገር የኤኮኖሚ እድገት ስትቲስቲክ እንዳሻ ቢደረደር ሕዝብን ከልመና፣ ከጎዳና ተዳዳሪነት፣ ከጦርነት አባዜ፣ ከድህነት ለመታደግ አልተቻለም። ከጥቂት ቀናት በፊት የአገዛዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ለምክር ቤት ተብዬ አባላት ባቀረበው ሪፖርት አማካይ የብሔራዊ ምርት በ9.7 በመቶ አደገ ተብሎ በሚነገርበት ሰዓት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በረሃብ እየተሰቃዩ መሆናቸው ግልጽ ሲሆን ሕዝቡ በተለያዩ ቀላልና ከባድ በሽታዎች እየተጠቃ መከላከያ ባላገኘበት፣ ንፁህ ውሃ ማግኘት ባልቻለበት፤ ከዚሁ ጋር የተያያዘውም ተገቢ የሆነ የመፀዳጃ ቦታ ለብዙሃኑ ባልተዳረሰበት በጤና ጉድለት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሰቃየ ባለበት፣ በብዙ ቦታዎች

የተለጠፉ የጤና ማስታወቂያዎችም ሆኑ የሚነገረው የእድገት አሃዝ ትርጉመ ቢስ ናቸው በማለት መፈረጁ የሚያስገርም አይሆንም። ሕይወተ ቢስ አሃዝ ሕይወትን እንደማያፈራ የበርካታ አፍሪካ ሀገራት ተመክሮም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነውና።

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና ሀገር ወዳዱንም የሚያበሳጨው በርካታ ዜጎቻችን በድርቅና በረሃብ ጥቃት የተነሳ ለባዕዳን እርጥባን ጠባቂነት የመዳረጉ ሁናቴ ቀጣይ የመሆኑና ያስከተለውን የማኅበራዊ ቀውስ አስከፊነቱን ሲገነዘብ ነው። ለዚህ ጉስቁልናና ችግር ተዳርጎ መታየት አላስችል ብሎት ቤተሰቡን ጥሎ መሰደድ ማሳፈሩ ቀርቶ በዘመናዊነት እየታየ ያለበት ነው። ለጋ ሴት ልጆችን ከዘመናዊ ባርነት አንስቶ ኢሰብዓዊ ለሆነ ተግባር እንዲሰማሩ እስከ መዳረግም የተደረሰበት ሁኔታ የእሴቶቻችንን መዝቀጥ አመላካች እንደሆነ ግልፅ ነው። እነዚሁ ሁሉ የአገዛዙ ፖሊሲዎች ያመጧቸው አሳዛኝ ክስተቶች ሊካዱ የማይችሉ የዘመናችን ቀጣይና ዘላቂ ችግሮች ናቸው። ለዚህም ነው በዚህ ሁናቴ እድገት ተግኝቷል እየተባለ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን ለማሞኘት የሚደረግ ጥረት ከመሆን ያላለፈና ራስንም ለትዝብት መጣል ነው በሚል እየተሰጠ ያለው አስተያየት በጥቂት የቀድሞ ሥርዓት አላሚዎችና በተቃዋሚ ምሁራን ሳይሆን በበርካታው ሕዝብ ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ በልመና፣ በረሃብና በጦርነት የታወቀችውን ኢትዮጵያ በእድገት ተርታ አስመዝግበን ታሪክ እንሰራለን ተብሎ በወያኔ አገዛዝ እየተለፈፈ ባለበት ሁኔታ ነው። በዚህም የተነሳ ነው ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ዛሬም እንደበፊቱ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ለማስከበር፤ በመልካም አስተዳደር ለመመራት፤ የገቢውን መጠን የሚያሳድግበት ስልት ለመቀየስና ሰላማዊና መልክ ያለው ኑሮ ለማግኘት አሁንም ሕዝባችን በከፍተኛ ናፍቆት የሚጠብቀው ብቻ ሳይሆን ለማሳካትም እየታገለ የሚገኘው።

ስለሆነም አንደኛው ዓመት በሌላ በተተካ ቁጥር መጪው ምን እንደሆነ ለመገመት የሚቻልበት ሁኔታ የተዘጋ ከመሆኑም በላይ የወያኔ የኤኮኖሚ ፖሊሲዎች እያስከተሏቸው ያሉ በርካታ የኑሮ ችግሮች ከዓመት ዓመት እየተሸጋገሩ ያሉ ብቻ ሳይሆኑ እየተባባሱም በመቀጠላቸው በይሻል ይሆናል የተሰፋ ኑሮ እንኳ ለመኖር ጭላንጭል ማየት የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል። የደብዛ ጭለማ አንዣብቦበት ይገኛል። በዚህም ሳቢያ ለችግሮቹ ቀጣይነት በሥልጣን ላይ ያለው አምባገነናዊ አገዛዝ በመሆኑ ከሱ መፍትሄ መጠበቅ ካቆመም አሥርተ አመታት አልፈዋል። በአባሪና በተባባሪነትም ከአገዛዙ ሥር የተኮለኮሉትን አስመልክቶማ እርባነቢስ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ስላረጋገጡለት በመጀመሪያ አካባቢ የነበረው ጭላንጭል ተስፋ እንኳ ያጨለሙበት በመሆናቸው ከእነሱ ምንም አይጠብቅም። የተወሰኑ ክፍሎች ደግሞ በተቃዋሚነት ሥም ትግሉን የሚያሸሞነሙኑ በእርባናቢስነት የታወቀ ምርጫ ተብዬ በተቃረበ ወቅት የወያኔን የተበላሸ ገፅታ ለማቆነጃጀት የሚርመሰመሱትን የትግሉ ደንቃራ ብሎ የፈረጃቸው ስለሆነ የሚጨነቅበት እንዳልሆነ የሚታይ ነው። በተለያዩ የፖለቲካና ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ተሸጉጠው አገዛዙን የጠሉ እያስመሰሉ በተግባር ግን የሱን መሰሪ ተንኮል በማራባትና ተግባራዊ ለማድረግ እየጣሩ ያሉትንም ከአገዛዙ የሚለዩበት ሁኔታ አልታይ እያለው ይልቁንም አንድ አካል አንድ መንፈስ እየሆኑበት በማግኘቱ ችግሩን የሚያቃልሉለት የመፍትሄ አካል ሳይሆኑ ይብሱኑ እያባባሱበት በመሆናቸው መጨነቁን ካቆመ ዓመታት አልፈዋል።

ባጠቃላይ እነዚህ ኃይሎች ሕዝባችን የራሱንም ሆነ የሀገሩን የወደፊት እጣ ለመወሰን እንዳይችል ጋሬጣ የደቀኑበት፤ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹን እንዳሻ የረገጡበት፤ የልቡንና ብሶቱን ተናግሮ ለችግሮቹ መፍትሄ እንዳያፈላልግ አፉን የለጎሙበት፤ ለመቃወም ሲሞክር ደግሞ እጣው ዘብጢያ፣ አለፍ ካለ ደግሞ

ደብዛውን በስውር ማጥፋት የተለመደ ተግባራቸው ነውና የሚወገዱበትን ስልት ከመንደፍ ውጪ ሌላ አማራጭ ሊኖረው አልተቻለውም።

የሕዝብ እኩልነት ዘበት ሆኖ ወያኔ በብሔረሰብ ላይ ተመስርቶ ያሰፈነው የክልል አገዛዝ ሀገሪቷን ለግንጠላና ፍጅት እያመቻቻት ነው። ዕድሜ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ላስተሳሰረው ታሪኩ እንጂ በወያኔ ሙከራማ ሀገራችን ብትንትኗ በወጣ ነበር። ያለው ሥርዓት ይዘቱ የእኩልነት ሳይሆን ጥርሱን ያገጠጠ ዘረኝነትና ልዩነት የሰፈነበት ነው። ወያኔ በቋንቋ ላይ ተመሥርቶ የገነባው የክልሎች አወቃቀር አንድነትን ከመፍጠር ይልቅ ለክፍፍል የተመቻቸ ሆኖ ተገኝቷል። የተወሰኑ አካባቢዎች ያለ ነዋሪው ፍላጎትና ይሁንታነት በግድ እንዲጠቃለሉ ተደርገው ለጭቆናና ለሁለተኛ ዜግነት ተዳርገዋል። ዜጎች በሰላም አብረው ተከባብረው እንዲኖር የሚያስችል ሳይሆን በተለያዩ አካባቢዎች እንደሚታየው ይበልጡኑ ለግጭቶች መሠረት ሆኖ የበርካታ ዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፤ የሕዝብ ኃብትና ንብረት ወድሟል። ለአካልና ለመንፈስ ጉዳት ተዳርገዋል። ከቀዬያቸው ተባረዋል። ተደጋግሞ እንደተገለፀው የማንኛውም ብሔረሰብ ድርጅት ኢትዮጵያዊነትን የማይወክል እንደሆነ ነው። ይህም ሲባል አለምክንያት አይደለም። ማንኛውም ብሔረሰብ በቁጥር ይነስ ይብዛ፤ በአሰራሩ ይጥበብ ይስፋ በብሔረሰብ ስም ፤ አስተሳሰብና እምነት ላይ ተመሥርቶ እስከተደራጀ ድረስ አሰያየሙና አስተሳሰቡ ባህሪውና ተግባሩ፤ ከመጠሪያው ጋር የሚሳሳቡ ውስጣዊ እንቅስቃሴውና የፖለቲካ ሕይወቱ ያንኑ አይነተኛ መከሰቻው የሆነውን ብሔረተኝነት የሚያጠናክሩ እየሆኑ ጉዞዉን ነው የሚቀጥለው። ላለፉት 23 ዓመታት የወያኔ የፌዴሬሽን ቀመር ተግባራዊ ሆኖ የተገኘው ተመክሮም የሚያመላክተውም ይህንኑ ነው። በወያኔ የበላይ ጠባቂነት ሕዝባችን የሚሉትን ያለነሱ ፍላጎትና ይሁንታነት ከጫንቃዎቹ እንዲቆናጠጡ አድርጎ ይህንን መከረኛ ሕዝብ በከፋ ደረጃ እየበዘበዙትና እየበደሉት ይገኛሉ። ታሪክን በማዛባት ላይ የተመሠረቱ የተወሰነ የመሬት አካባቢዎች በይገባኛል ጥያቄ ግጭቶች እየተፈጠሩ አዳዲስ ቅራኔዎች እየተከሰቱ መኖር የሌለባቸው ልዩነቶችን በሕዝቡ መካከል ሰርገው እንዲገቡ እየተደረገ ነው። የይስሙላ እንኳን ያለ በላይ ጠባቂያቸው የክልል ባለሥልጣናት በክልላቸው የመወሰን ሥልጣን የላቸውም። በመሆኑም የመላ ኢትዮጵያውን ሕዝብ መብትና ነፃነትን ለመጠበቅ፤ ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለማራመድና ለማሟላት፤ በእኩልነት ላይ ለምትመሠረት ኢትዮጵያ ሀገራችን በጋራ በአንድነት ለመቆም የሚያስችል ሁናቴ እስካልተፈጠረ ድረስ ደግሞ ችግሩ ቀጣይ ለመሆኑ የማይታበል ነው።

ያለፈ ታሪክ የወደፊቱ መስታወት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ የሚመጣውን የዛሬው ተግባራችን ይወስነዋል ይባላልና 41 ሚያዚያዎችን አገባዶ 42ኛውን ለመሸኘት በሚገኝበት ወር ኢሕአፓ ከላይ በሰፋት የተዘረዘሩት፤ ለድርጅቱ መመሥረትና በቀጣይነት በፅናት ለመታገል መሠረት የሆኑት፤ በየካቲቱ 66 ከሕዝብ ጋር አንስቶ በሰፋት የተንቀሳቀሰባቸው ጥያቄዎች ዛሬም ከ42 አመታት በኋላ ምላሽ አለማግኘታቸው በአሁኑ ወቅት ሕዝባችን ለሚገኝበት ሁናቴ የሚመሰክሩ ናቸው። በርግጥም ከዛሬ 42 ዓመት በፊት የነበረው የፖለቲካ ፤ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ የግዴታ ይህንን ድርጅት በአንጋፋነት አምጦ መውለድ የነበረበት እንደሆነ ታሪክን ጥላሸት ለመቀባት የሚግደረደሩ ካልሆኑት በስተቀር የሕዝባችንን የትግል ታሪክ በቅርበት የሚከታተሉ የፖለቲካ ሊቃውንትና የሥነምግባር ተመራማሪዎች ሁሉ የሚስማሙበት ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ ችግሩንና መከራውን አብሮ እየተቋደሰ መጥፎውኑም ሆነ መልካሙን አብሮ እያሳለፈ የሚገኘው ሕዝባችን የሚመሰክረው ነው። የችግሮቹ ቀጣይነት መላ ሕዝቡን በማመሰቃቀል የሚታዩና በሕዝቡ ፍላጎት መፍትሄ የሚሹ ናቸው። ካለፉት በባሰ ደረጃ ቀጣይ እንዲሆኑ

በዋና ተጠያቂነት ተፈጥሞ ያለው ደግሞ የወያኔ አምባገነንና ኀጠኛ አገዛዝ ነው። ስለዚህም ነው ሕዝብ አግባብነት አላቸው ብሎ በሚያምንባቸው የትግል ስልቶች አገዛዙን ከሥልጣኑ ማስወገድ የግዴታ የሚሆነው። የትግሉ መሠረታዊ ዓላማ ምንና ለምንስ እንደሆነ በማጠየቂያነት የግዴታ እየቀረቡ የሚገኙትም በዚሁ ምክንያት እንጂ በሌላ አይደለም።

ሕዝባችንም በትግሉ መወገድ ያለበት ዋነኛ ጠላቱ ማን እንደሆነ እያረጋገጠና መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት እየከፈለ  መሆኑን እያደረጋቸው ባሉት እንቅስቃሴዎቹ ግልፅ እያደረገ ነው። በዚህ ላይ ምንም አይነት ብዥታ የለበትም። ጭንቀትና ብዥታ ያለባቸው በጫንቃው ላይ ለመቆናጠጥ የሚቋምጡ ቡድኖች ብቻ ናቸው። በዚህ አቋማቸውም ስልፋቸው ከአገዛዙ ጋር መሆኑን እያበሰሩ ያሉበት፤  ከታሪክ ጋርም የተላተሙም ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን ለባርነትና ለጭቆና ሰለባነት ለመዳረግ ዳዴም የሚሉ ናቸው። ለዚህም ነው አገዛዙንና የመሠረተውን ሥርዓት የራሱን ሕገ-አገዛዝ በመጠቀም በጥገና ሂደት ማስተካከል ይቻላል በሚል ከሱ ጋር የተቃቀፉና ሶስተኛ አማራጭ በማለት ጥቂቶች ሲያቀነቅኑ እንደነበሩት ሕይወተ ቢስና አሳፋሪ መሆናቸውንና ሊሰራም እንደማይችል ባለፉት 22 አመታት በችግሮቹ ቀጣይነት የተስተዋለ ነው። ይህም የሕዝብ ፍላጎት የሆነውን መሠረታዊ የለውጥ መንገድ ተቃርኖ መገኘት በመሆኑም በብዙሃኑ ዘንድ ተቀባይነት እያጣ ለመሄዱም በትግሉ ሂደት በግልፅ የታየ ነው።

ለዚህም ነው ከፊታችን ቀርቦ ያለው ምርጫ አንድና አንድ ብቻ ነው ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት ሁናቴ እየተገለፀ የሚገኘው። ይህም ምስጢር ሳይሆን የሰፊውን ሕብረተሰብ ክፍል እንቅስቃሴ በሚያጠናክሩና በሚያስተባብሩ ጥያቄዎች ዙሪያ ማታገል፤ ማደራጀት፤ አቅጣጫ ማሳየት፤ አመራር መስጠት ሲሆን በዚህም ትግሉ ከማን ጋር የሚለውን የመተባበር ጥያቄ ምላሽ ሰጪና የትኩረቱንም አቅጣጫ ጠቋሚነት በሚገባ ተገንዝቦ መጓዝን ነው። ባጭሩ የሁሉም ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆነ ኃይል ሁሉ ትኩረቱ ወደ ሕዝብና ከሕዝብ ጋር አሣና ውሃ መሆኑ ላይ ነው። ይህም ብቻ አይደለም። በተናጠል መጓዝና የሕዝብን ፍላጎት ስኬታማ ለማያደርግ ለታሪክ ሽሚያ መንፈራገጡ ጀርባን መምለጥ፤ ለሕዝብ አላስፈላጊ ጉዳትን ማስከተል መሆኑ ያለፉት ዓመታት በሚገባ ያመላከቱት አካሄድ ነው። ይህንንም ተገንዝቦ ለአገዛዙ ድርጊቶች የሚመጥኑ ሁለገብ ስልቶችን እንደወቅቱና ሁኔታው አስፈላጊነት ተግባራዊ ማድረግ የግድ ነው።